# አዲሱንና ጊዜያዊ የሆነውን የሰብዓዊ ስደተኞች ኤሴሳይ (SSI) ቅጥያ ሕግን በተመለከተ አንድ ጠበቃ ያወጣው መምሪያ

## *ከኦክቶበር 1 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለ*

ተጨማሪ የደህንነት ገቢ ወይም SSI ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው አዛውንቶችና ለአካለስንኩል ሰዎች ተጨማሪ የገቢ እርዳታ ያቀርባል። ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ለስደተኞችና ለአንዳንድ ሌሎች ሰብዓዊ ስደተኞች የተሰጡት የ SSI ጥቅማጥቅሞች የተወሰኑ ሲሆኑ የተሰጡትም ለሰባት ዓመት ያህል ብቻ ነው። "The SSI Extension for Elderly and Disabled Refugees Act" ወይም "ለአዛውንትና ለአካለስንኩል ስደተኞች የወጣው የኤስኤስአይ ቅጥያ ሕግ" (የሕዝብ ሕግ 110-328) የሚባለው አዲስ ሕግ እነዚህ ስደተኞች የ SSI ጥቅማጥቅሞች እንዲያገኙ የሚያደርግና ጥቅማጥቅሞቹን ቢያንስ በተጨማሪ ለሁለት ዓመት እራዝምላቸው ማግኘት እንዲቀጥሉ የሚያደርግ ሕግ ነው።

የሶሻል ሴክዩሪቲ አስተዳደር (SSA) ይህ ሕግ እንዴት መፈፈጸም እንዳለበት የሚያብራራ የውስጥ አመራር አውጥቷል። የዚህ አመራር ስም Emergency Message 08105 SEN ወይም ድንገተኛ መልዕክት 08105 SEN (ባጭሩ እዚህ "EM" ተብሎ ነው የሚጠራው)። ይህ EM በ POMS SI 00502.107 ውስጥ ይገኛል፣ ሆኖም የሶሻል ሴክዩሪቲ አስተዳደር ድህረገጽ ላይ ይህ መምሪያ እስከተጻፈበት ቀን ድረስ አይገኝም።

ይህ ጽሑፍ አዲሱ ሕግን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን አቀነባብሮ ይዟል። በሚያስፈልግ ጊዜ ከ EM ጥቅስ ይዞ ቀርቧል።

1. **በሰባት ዓመት ገደብ ምክንያት SSI ዬን አጣሁኝ። ይህ ሕግ እኔን ይጠቅመኛል? (ከዚህ በፊት ለSSI አመልክተው የማያውቁ ከሆነ ጥያቄ ቁጥር 6ን ይመልከቱ)**

ከሚከተሉት ሁኔታውች ውስጥ አንዱ እርስዎን የሚመለከት ከሆነ ለጠቅምዎት ይችላል፦

**ሀ) ዕድሜዎ ከ18 በታች ወይም ከ70 በላይ ነው።**

ለምሳሌ፦ አሜሪካን አገር በሴፕቴምበር 1996 የመጣች አንዲት ሴት SSI ለሰባት ዓመት ካገኘች በኋላ በኦክቶበር 2003 አጣችው። አሁን ዕድሜዋ ከ70 ዓመት በላይ ከሆነ ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ ሁለት ዓመት SSI ማግኘት ትችል ይሆናል። የአሜሪካ ዜግነት ለማግኘት አመልክታ እስከ ኦክቶበር 2010 ዓ.ም. አሁንም ያላገኘችው ከሆነ SSI ለሶስተኛ ዓመት ማግኘት ትችላለች።

**ለ) ግሪን ካርድ ካገኙ ስድስት ዓመት አልሞላዎትም።**

ለምሳሌ፦ በኦክቶበር 1998 ዓ.ም. አሳይለም ያገኘ አንድ ሰው በኖቬምበር 1998 ዓ.ም. የአካለስንኩልነት SSI ማግኘት ጀመሮ አሳይለም ካገኘ ከሰባት ዓመት በኋላ በኖቬምበር 2005 ዓ.ም. አቆመ። በኖቬምበር 1999 ዓ.ም. ግሪን ካርድ ለማግኘት ማመልከቻ አስገብቶ፣ ከብዙ መዘግየት በኋላ ግሪን ካርዱን በመጨረሻ በ ጃንዋሪ 2004 ዓ.ም. አገኘ። ይህ ሰው ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተጨማሪ ሁለት ዓመታት SSI ማግኘት ይችል ይሆናል፣ እንዲሁም ለአሜርካ ዜግነት ማመልከቻ ከኦክቶበር 2010 ዓ.ም. በፊት እስካስገባ ድረስ ለተጨማሪ ሶስተኛ ዓመት SSI ማግኘት ይችል ይሆናል።

**ሐ) ግሪን ካርድ ለማግኘት ማመልከቻ ያስገቡት SSI ማግኘት ከጀመሩ ከአራት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ነው።**

ለምሳሌ፦ በፌብሩዋሪ 1999 ዓ.ም. አሜሪካ የመጣች ስደተኛ ዕድሜዋ 55 ዓመት ሲሆናት በ2000 ዓ.ም. SSI ማግኘት ጀመረች። በ2003 ለግሪን ካርድ ማመልከቻ አስገብታ ግሪን ካርድዋን አገኘች። (LPR የምትሆነው አሜሪካን አገር ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ ፌብሩዋሪ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ነው)። በሰባት ዓመቱ ሕግ ምክንያት የ SSI ጥቅማጥቅሞችዋ በማርች 2006 ዓ.ም. አለቁ። አሁን ዕድሜዋ 63 ዓመት ሲሆን ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት

**Amharic**

ድረስ SSI ማግኘት ትችላለች። የዜግነት ማመልከቻ ከኦክቶበር 2010 ዓ.ም. በፊት እስካስገባች ድረስ ተጨማሪ ሶስተኛ ዓመት ማግኘት ትችላለች።

**መ) የገቡት በኩባ ወይ በሃይቲ በኩል ነው።**

ለምሳሌ፦ በሜይ 1997 ዓ.ም. አንድ ሰው በኩባ ወይም በሃይቲ በኩል ገቢ ተባለ። በአካለስንኩልነት ምክንያት በ2000 ዓ.ም. SSI ማግኘት ጀመረ፣ እስከ ጁን 2004 ዓ.ም. ማግኘቱን ቀጠለና ያን ጊዜ ተፈጸመ። አሁን ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተጨማሪ ሁለት ዓመታት SSI ማግኘት ይቀጥላል፣ ለአሜሪካ ዜግነት ከኦክቶበር 2010 ዓ.ም. በፊት ማመልከቻ እስካስገባ ድረስ ሶስተኛ ዓመት ይጨመርለታል።

**ሠ) ከአገር እንዲባረሩ ተላልፎ የነበረው ውሳኔ ተነስቶልዎታል።**

ለምሳሌ፦ አንዲት ሴት ከአገር እንድትባረር ተላልፎባት የነበረው ውሳኔ በዲሴምበር 1996 ዓ.ም. ተነሳላት። በአካለስንኩልነት ምክንያት SSI በጃኑዋሪ 1997 ዓ.ም. ማግኘት ጀምራ በጃኑዋሪ 2003 ዓ.ም. ተፈጸመ። ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተጨማሪ ሁለት ዓመታት ድረስ SSI ማግኘት ትችላለች። ለአሜሪካ ዜግነት ማመልከት ስለማትችል ሶስተኛ ዓመት መቀጠል አትችልም።

**ረ) የአሜሪካ ዜግነት ለማግኘት ማመልከቻ አስገብተዋል ወይም የቃለ መሃላ ስነሥርዓት ላይ ለመሳተፍ ቀጠሮዎን እየጠበቁ**

ለምሳሌ፦ አንድ ሰው አሜሪካን አገር ስደተኛ ሆኖ በዲሴምበር 1998 ዓ.ም. መጣና በጃኑዋሪ 2000 ዓ.ም. ዕድሜው 65 ሲሆን SSI ማግኘት ጀመረ። በሰባት ዓመት የጊዜ ገደብ ምክንያት በጃኑዋሪ 2006 ዓ.ም. SSI ማግኘት አቆመ። በዲሴምበር 2005 ዓ.ም. ለአሜሪካ ዜግነት ማመልከቻ አስገባና በዲሴምበር 2006 ለኢንተርቪው ተጠራ። ለዜግነት በቀበሉትም እስካሁን ሰርተፊኬቱን አላገኘም ምክንያቱም የግል ታሪክ ምርመራ ሲደረግ ዘገየ። ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተጨማሪ ሁለት ዓመታት ድረስ SSI ማግኘት ይችላል፣ ዜግነቱን እስከዚያው ካላገኘ ሶስተኛ ዓመት መቀጠል ይችላል። (ማሳሰቢያ፦ ይህ ሰው በክፍል ሀ ስርም ተቀባይነት ይኖረዋል)።

*[EM አንቀጽ §B(3)-(4)] ን ይመልከቱ*

**2. በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክንያት SSI ያጡ ሰዎች በሙሉ በአዲሱ ሕግ መሠረት ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች ማግኘት ይችላሉ?**

አይችሉም። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ክፍሎች የማይመለከታቸው ሰብዓዊ ስደተኞች ተጨማሪ ሁለት ዓመት ማግኘት አይችሉም። ለምሳሌ፦ አንዲት በኦክቶበር 1998 ዓ.ም. በ33 ዓመት ዕድሜዋ አሜሪካን አገር መጥታ በ1999 ዓ.ም. ግሪን ካርድዋን ያገኘች ስደተኛ (ከመጣች ከአንድ ዓመት በኋላ) በአካለስንኩልነት ምክንያት ዕድሜዋ 35 ሲሆን SSI ማግኘት ትጀምራለች። SSI ዋን በኖቬምበር 2005 ዓ.ም. ታጣለች፣ ዕድሜዋም አሁን 43 ነው። ለዜግነት እስካሁን አላመለከተችም። ይህንን እስከምታደርግ ድረስ አዲሱ ሕግ ለሷ አይሠራም ምክንያቱም ከስድስት ዓመት በላይ LPR ሆናለች።

**3. SSI ከተቋረጠብኝ በኋላ ለስንት ተጨማሪ ዓመታት ማግኘት እችላለሁ?**

ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ ከኦክቶበር 1 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ሌላ ሁለት ዓመት SSI ማግኘት ይችላሉ። የዛን ጊዜ ሲቲዝን ካልሆኑ፣ ሆኖም የዜግነት መቀበያ ማመልከቻ አስገብተው በመጠበቅ ላይ ያሉ ከሆነ፣ እስከ ሴምፕቴምበር 30 2011 ዓ.ም. ድረስ ተጨማሪ ሶስተኛ ዓመት SSI ማግኘት ይችላሉ። *[EM አንቀጽ §B(4)]*

**4. የSSI ጥቅማጥቅሞቼ ለመጀመር ምን ማድረግ አለብኝ?**

SSA ብቁ የሆኑ በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገድብ ምክንያት SSIያቸውን ያጡ ሰብዓዊ ስደተኞችን እራሱ ጥቅማጥቅማቸውን እንደሚያድስ አስታውቋል። ሆኖም፣ SSA ይህንን መቼ እንደሚያደርግ አናውቅም። ስለዚህ በፍጥነት በአካባቢዎ ወደሚገኘው የሶሻል ሴክዩሪቲ የአውራጃ ቢሮ እራስዎ ሄደው SSI መቼ እንደሚታደስ እንድትጠይቁ እናሳስባለን። ከፈለጉ SSA ጋር በስልክ ቁጥር 1-800-772-1213 መደወል ይችላሉ። መስማት የሚሳንዎት ከሆነ መስማት ለሚሳናቸው ሰዎች የተዘጋጀው መስመር ጋር በስልክ ቁጥር 1-800-325-0778 ይደውሉ።

የ SSI ጥቅማጥቅሞችዎ የቆሙት በኦክቶበር ወይም በኖቬምበር 2008 ዓ.ም. ከሆነና ቤሮው ድረስ ሄድው እንዲታደስልዎት ከጠየቁ SSA ወዲያው ማደስ አለበት። *[EM አንቀጽ §D]* ከዲሴምበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የሕጉን ቅጥያ መጠቀም የሚችሉ ስደተኞች በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክንያት SSI ያቸውን ማጣት የለባቸውም። ቢያንስ ለተጨማሪ ሁለት ዓመት ጥቅማጥቅም ማግኘት መቀጠል ይችላሉ።

የ SSI ጥቅማጥቅሞችዎ የቆሙት ከኦክቶበር 1 2008 ዓ.ም. በፊት ከሆነ SSA ገቢዎ ብቁ እንደሚያደርግዎት ለማረጋገጥ ከኦክቶበር 1 2008 ዓ.ም. በኋላ ለማንኛውም ወር የገቢ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፣ እንዲሁም LPR ወይም ለዜግነት እንዳመለከቱ ማረጋገጫ ይጠይቅ ይሆናል። ሕጉ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ነገሮች እንደሚያሟሉ የሚመሰክር ሰለ ኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ማረጋገጫ ከሌልዎት፣ SSA ወረቀት ያስፈርምዎትና ስለኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ያጣራል። *[EM አንቀጽ § E(4)-(12)]* ከኦክቶበር 1 2008 ዓ.ም. በኋላ ያልዎትንም የገቢ ማረጋገጫ ያጣራል። *[EM አንቀጽ § E(12)]* እስከዛ ቀን ድረስ ማረጋገጫ ካቀረቡ፣ SSA ጥቅማጥቅሞችዎን ወደኋላ ሄዶ ከኦክቶበር 1 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በማንኛውም ቀን ማረጋገጫውን ቢያቀርቡም። አለበለዚያ SSI የሚያገኙት ማረጋገጫ ለሚያቀርቡባቸው ወራት ብቻ ነው። *[EM አንቀጽ § D(12)]* ስለ አዲስ ተመዝጋቢዎች በይበልጥ መረጃ ለማግኘት ጥያቄ 7ን ይመልከቱ።

5. **በአካለስንኩልነት ምክንያት SSI አገኝ ነበር ሆኖም በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክንያት አልቋል። SSI እንደገና ለማግኘት አካለስንኩል መሆኔን ማረጋገጫ ማቅረብ አለብኝ?**

የለብዎትም። በተለምዶ SSA ከአንድ ዓመት በላይ SSI ሳያገኙ የቆዩ አካለስንኩል ግለሰቦች የ SSI ጥቅማጥቅሞቻቸው ከመታደሳቸው በፊት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። ሆኖም አሁን ግን SSA ግለሰቦች SSIያቸውን ለማሳደስ የአካለስንኩልነት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ አይጠይቅም። *[EM አንቀጽ § C]* ማሳሰቢያ፦ አዲስ በአካለስንኩልነት ምክንያት ለ SSI የሚያመለክቱ ግለሰቦች ግን ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

6. **የ SSI ጥቅማጥቅም አሁንም አገኛለሁ፣ ሆኖም የሰባት ዓመት የጊዜ ገደብ ይመለከተኛል። SSIን ለተጨማሪ ሁለት ዓመት እንዳገኝ ማድረግ ያለብኝ ነገር አለ?**

የለብዎትም። የሰባት ዓመቱ ገደብ እርስዎን የሚመለከትዎት ከሆነ ግን አሁን SSI እያገኙ ከሆነ አሁን ምንም ተጨማሪ ነገር ማድረግ የለብዎትም። ወደፊት SSA "የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን እየጣርኩ ነው" የሚል መግለጫ እንዲፈርሙ ይጠይቅዎት ይሆናል። በተረፈ ግን የቅጥያ ሕጉ እርስዎን የሚመለከት ከሆነ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ የለብዎትም። SSA በቀጥታ SSI ዎን ያድስልዎታል። SSI የሚያገኙት ባጠቃላይ ለዘጠኝ ዓመት ይሆናል። ዘጠኙ ዓመት ከኦክቶበር 2011 ዓ.ም. በፊት ካለቀና የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ አስገብተው በመጠበቅ ላይ እያሉ ከሆነ ግን እስከ ኦክቶበር 2011 ዓ.ም. ድረስ SSI ማግኘት መቀጠል ይችላሉ።

ጥቅማጥቅማቸው በኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ወይም በኖቬምበር 2008 ዓ.ም. የሚያልቅ ሰዎች መሃል ላይ ጥቅማጥቅሞቻቸው ሊቋረጡ ይችላል። ወዲያው ግን መታደስ ይገባቸዋል። የ SSI ጥቅማጥቅሞችዎን ወዲያው ለማሳደስ SSA ን ይገናኙ። የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችዎ በስህተት ከተቋረጡ የስቴት ድርጅትዎንም መገናኘት ይኖርብዎት ይሆናል። የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችዎን ለማቋረጥ ምንም ዓይነት ሙከራ ከተደረገ አቤቱታ ያስገቡ።

7. **በቅርቡ ዕድሜዬ 65 ሆነ ወይም አካለስንኩል ሆንኩኝ። በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክንያት SSI ማግኘት አትችልም/አትችይም ተባልኩኝ። ከዚህ በፊት መቼም SSI አግኝቼ አላውቅም። አዲሱ ሕግ ሊረዳኝ ይችላል?**

በኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ወይም ከዛ በኋላ SSI ለማግኘት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ በአሳይለም የገቡ ሰዎች፣ ሬፍዩጂዎችና ሌሎች የተወሰኑ ሰብዓዊ ስደተኞች፣ መጀመሪያ ሬፍዩጂ፣ አሳይለም የተሰጣቸው ወይም ስደተኛ የሆኑበት ዓመት ታይቶ SSI ሊያገኙ ይችሉ ይኖናል፦

- ጊዜው ከ ኦክቶበር 2002 ዓ.ም. በኋላ ከሆነ እስከ ኦክቶበር 2011 ዓ.ም. ድረስ ጥቅማጥቅም ማግኘት ይችሉ ይሆናል።
- ጊዜው ከኦክቶበር 1999 ዓ.ም እስከ ኦክቶበር 2002 ዓ.ም. መሃል ባለው ውስጥ ከሆነ፣ SSI ማግኘት የሚችሉት ለ SSI ማመልከቻ ካስገቡበት ቀን ጀምሮ ሬፍዩጂ፣ አሳይለም ከተሰጥዎት ወይም ሰብዓዊ ስደተኛ ከሆኑበት ቀን እስከ ዘጠኝ ዓመት ጊዜ ድረስ ነው። ይህ ጊዜ ካለቀ በኋላ የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ አስገብተው እየጠበቁ ከሆነ ወይም የአሜሪካ ዜጋ ከሆኑ ብቻ ነው እስከ ኦክቶበር 2011 ዓ.ም. SSI መቀበል መቀጠል ይችላሉ።
- ጊዜው ከኦክቶበር 1999 ዓ.ም. በፊት ከሆነ SSI ቀጥታ ማግኘት አይችሉም።

ያስታውሱ፦ እነዚህ ልዩ ሕጎች የሚመለከቱት ኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ላይ ወይም ከዚያ በኋላ ለ SSI ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ስደተኞችን ብቻ ነው።

8. **ከዘጠኝ ዓመት በኋላ አሁንም የአሜሪካ ዜጋ ካልሆንኩኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ለተጨማሪ ሁለት ዓመታት SSI ከደረስዎት በኋላ አሁንም የአሜሪካ ዜጋ ካልሆኑና ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ አስገብተው እየጠበቁ ከሆነ ለሶስተኛ ዓመት SSI ማግኘት ይችላሉ። ሆኖም ከሴፕቴምበር 30 2011 ዓ.ም. በኋላ ጥቅማጥቅም ማግኘት አይችሉም። SSI ማግኘት እንዲቀጥሉ ኮንግሬስ አዲስ ሕግ ካልደነገገ በስተቀር ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት።

9. **ከዚህ በፊት በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክኒያት የሶሻል ኬክዩሪቲ ቢሮ SSIዬን አስቁሞብኛል። ያንን ጊዜ መተኪያ SSI ማግኘት እችላለሁ?**

አይችሉም፣ ሆኖም ከኦክቶበር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተጨማሪ ሁለት ዓመታት ድረስ SSI ማግኘት ይችላሉ። SSI ማግኘት ያቆሙት በሰባት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ምክንያት ከሆነ ወደኋላ ተኬዶ ከኦክቶበር 2008ዓ.ም. እስከ ኦክቶበር 2010 ዓ.ም. ደረስ SSI ማግኘት ይችላሉ። ሆኖም፣ ከዚያ ቀደም ላሉት ወራት SSA ምንም ዓይነት የ SSI ጥቅማጥቅሞች አይሰጥዎትም።

10. **የSSI ጥቅማጥቅሞቼን ለማሳደስ በአካባቢዬ ወደሚገኘው የ SSA ቢሮ ሄጄ ነበር ግን ብቁ አይደለህም/አይደለሽም ተባልኩኝ። ይህ መምሪያ ላይ ባለው መረጃ መሠረት ግን ብቁ ነኝ ብዬ አምናለሁ። ምን ማድረግ እችላለሁ?**

በአካባቢዎ ወደሚገኘው የሕግ አገልግሎቶች ቢሮ ጋር ባስቸኳይ ይደውሉ። እዚያ ያለ ሰው ሊረዳዎት ይችላል።

11. **የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን የእንግሊዝኛና የዜግነት ፈተና መውሰድ አለብኝ?**

ይህ አዲስ ሕግ የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን መከተል ያለብዎትን አይቀይርም። ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ካልሆነ በስተቀር፣ የሶሻል ሴክዩሪቲ ቢሮ አካልዎና አእምሮዎ እስከፈቀደው ድረስ "የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን እየጣርኩ ነው" የሚል መግለጫ ያስፈርምዎታል። እንግሊዝኛ ከመማር የሚያግድዎት ዓይነት አካለስንኩልነት ካልዎት ከኢሚግሬሽን ባለሞያ ጋር ይወያዩ። መንግሥት የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የታሪክና የመንግሥት ፈተናዎች እንዳይወስዱ ፈቃድ ሊሰጥዎት ይችላል።

**Amharic**

**12. ግሪን ካርድ ለማግኘት ወይም የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን ማመልከቻ ካስገባሁ ከስድስት ወር በላይ ሆኖኛል። የአሜሪካ ዜግነትና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (U.S. Citizenship and Immigration Services (CIS)) ማመልከቻዬን እንዲያፋጥንልኝ ማድረግ የምችለው ነገር አለ?**

አዎን። በቅርቡ በካፕላንና በቸርቶፍ መካከል በቀረበው ክሥ አማክኝነት፣ የሰባት ዓመቱ ሕግ የሚመለከታቸው ስደተኞች ማመልከቻቸው እንዲፋጠን ማድረግ ይችላሉ። ከስድስት ወር በላይ ጠብቀው ከሆነ፣ CIS ጋር በስልክ ቁጥር 1-800-889-4369 ይደውሉና ማመልከቻዎ እንዲፋጠን ይጠይቁ። ይህ የተፋጠነ ሂደት አዲሱ ሕግ ከወጣ በኋላም በሥራ ላይ አለ።

ለግሪን ካርድዎ ወይም ለዜግነትዎ ገና ማመልከቻ ካላስገቡ፣ ማመልከቻዎን ሲያስገቡ መፋጠን እንዳለበት ምክንያቱም "<u>ካፕላን</u> ክላስ" ውስጥ ስለሆኑ እንደሆነ ለ CIS ይናገሩ።

**13. ለግሪን ካርድ ወይም ለዜግነት ለማመልከት የገንዘብ አቅሙ የለኝም። ማግኘት የምችለው እርዳታ አለ?**

አዎን። በቅርቡ በካፕላንና በቸርቶፍ መካከል በቀረበው ክሥ አማክኝነት፣ SSIያቸው የጊዜ ገደብ ያለበት ስደተኞች የማመልከቻው ገንዘብ ይሰረዝልኝ ብለው ከጠየቁ ሊሰረዝላቸው ይችላል። የግሪን ካርድ ወይም የዜግነት ማመልከቻ ሲያስገቡ "ክፍያ መሻሪያ" ("fee waiver" )ይጠይቁ፣ ለአሜሪካ ዜግነትና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶችም (U.S. Citizenship and Immigration Services (CIS)) "የ<u>ካፕላን</u> ክላስ" ውስጥ እንደሆኑ ይግለጹ።

| |
|---|
| ተጨማሪ ጥያቄ ካልዎትና እርዳታ ለማግኘት እባክዎን የአካባቢዎን የሕግ አገልግሎቶች ቢሮ፣ የሕግ እርዳታ ቢሮ ወይም የጥብቅና ድርጅትን ይገናኙ። |

**Amharic**